> ***** ሾልኮ የወጣ የአርበኞች ግንቦት 7 ምክር ቤት አባል እይታ ህዝብና አባላት እንዲፈርደው የተጻፈ*****

ክፍል 2

21/03/2018

ባለፈው ሳምንት ከውጪ ወደ አስመራ የገባው የአርበኞች ግንቦት 7 አባላቶች ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አጭር ና ማስፈራራት የሞላበት ስብሰባ ተጠናቆ የኤርትራ መንግስት ወደ አዘጋጀልን ሆቴል በስጋት እና ጥርጣሬ መንቀሳቀሳችንን ጠቅሼ ነበር ያቆምኩት።

ከአደርንበት ሆቴል በጠዋት ተነሳሁና ወደ ቁርስ አዳራሽ ሄድኩ ብቻዬን አልነበርኩም ከውጪ የመጡት የትግል አጋሮቼ ጋር የተዘጋጀልንን እንቁላል ጥብስና እንደየ ምርጫችን ቡናና ሻይ አዘን ተቋደስን።

በወቅቱ የተመለከትኩት አስገራሚ ነገር እኛን የሚቆጣጠሩ የደህንነት ክፍል ተብለው በዶክተር ብርሓኑ ነጋ በእኛ ላይ መብት የተሰጣቸው እስኪመስል ሰብሰብ ባልንበት የምግብ ጠረቤዛ ላይ በመምጣት ትዕዛዝ በተሞላበት ድምጽ አጭር ስብሰባ ሰላለን ወደ ቢሮ አካባቢ እንጠብቃችኋለን ብለወን ከቁርስ በኋላ ወደዛው አመራን።

ከመሰብሰቢያው ቦታ የደረስኩት ዘግይቼ ነበር ።

በቁጥር ሶስትና አራት የሚሆኑ  በተደጋጋሚ በየቦታው ሲከታተሉን ከነበሩት አንድ ፈርጠም ያለ ግን ደግሞ ለማንም አክብሮት የሌለው ተንደርድሮ መጣና " ማነህ ትናንት መሪያችን ሰዓት እንድታከብር ደጋግሞ የነገረህ መሰለኝ ተግባባን" ብሎኝ መልሴን ሳይሰማ ወደ ሌላኛው አርፋጅ ተንደረደረ።

መድረክ ብጤ ተዘጋጅቷል ፣ከተዘጋጀልን ወይም ከነበሩት ወንበሮች ላይ ተቀምጠን በትኩረት ማዳመጥ ጀመርን

" ሁላችሁም እንደምታውቁት የያዝነው ትግል እጅግ በጣም መራርና በርካታ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ነው።

ስለሆነም ማናችሁም እገሌ ተገሌ የሚባል ነገር የለም ቪዲዮ መቅረጽ፣ፎቶግራፍ ማንሳት ፣ቴክስት መላላክ ፣ወይም መደወልና መልዕክት መላላክ ፍጹም የተከለከሉ ከመሆናቸውም በላይ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ይዞ የተገኘ አባልም ይሁን ደጋፊ ላይ እርምጃ እንድንወስድ ትዕዛዝ ተቀብለናል በመሆኑም ያላችሁን ሞባይልም ሆነ ካሜራ በአደራ መልክ ካረፋችሁበት ሆቴል እያስመዝግባችሁ እንድታስቀምጡ በጥብቅ እናሳስባለን" በማለት ከጥቂት ዲስኩር ጋር ቀላቅሎ አስጠነቀቀን።

በሶስተኛው ቀን በጠዋት ተነስተን ለመጓዝ ተዘጋጀን በአስተናጋጆቻችን መዘግየት ምክናየት በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 5 ሰዓት ከምሳ በፊት ማለት ነው ሁለት አውቶቢስ ከአረፍንበት ሆቴል በር ላይ ቆሞ እየተፈተሸን ስንገባ ሞባይል በስህተት ይዘው የተገኙ አባሎችን ካረፉበት ሆቴል አስመዝግበው እንዲያስቀምጡ በማመናጨቅ አሶረዷቸው።

ሲመለሱ በድጋሜ ከማስጠንቀቂያ ጋር እየተፈተሹ ገቡ ።

ሁለቱ አውቶቢሶች በሁለት ፒካፕ ቶዮታ መኪናዎች ታጅቦ ጉዞ ብንጀምርም ፈታ ብለን እያወራን መሄድ አልቻልንም ።

ዶክተር ብርሓኑ ነጋ ከቅርብ ጓደኞቹ ጋር በራሱ አሽከርካሪነት አንድ ፒካፕ ይዟል።ከረጅም ጉዞ በኋላ ባሪንቱ ደርሰን ምሳ በላን ግን

አሁንም ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ የደህንነት አባላት እይታ እንድንወጣ አልተፈቀደልንም ።

ከታሰበው የሃይኮታ ከተማ ወጣ ብሎ ከሚገኘው የሱዳኑ ጆን ጋራንግ አማጺያን ቡድን መሪ ከሰለጠነበት ማሰልጠኛ ደረስን። ማሰልጠኛው ሙሉ ማረፊያ ቦታ አለው ሰፊም ነው።

ከማሰልጠኛው አቀባበል ተደረገልን ግን አሁንም አካባቢው በባንዲራችን ከመድመቁ ባሻገር ያካባቢው ሙቀት በጣም ሃይለኛ ነበር።

ከአስመራ በሁለት አውቶቢስና በሁለት ፒካፕ ታጅቦ የመጣው የስብሰባ ታዳሚ አቀባበል ተደርጎልን እራት ከተጋበዝን በኋላ መደዳውን ወደ ተዘረጋው ፍራሽ በመሄድ አረፍ ካልንበት አንዱ ሰልጣኝ ወታደር ከመሃላችን በመግባቱ የዶክተር ብርሃኑ የደህንነት ክፍል አፋፍሰው ወሰዱት።

ታጋዩ ወንድማችን ከተናገረው ቃላት ውስጥ ትዝ የሚለኝ “ለምን እኛን ሊያዩን የመጡ ናቸው ለምን ልዩነት ትፈጥራላችሁ” እያለ ተጎትቶና ታጅቦ ከመሃላችን ተወሰደ።

ቸር ይግጠመን

በቀጣዩ ሳምንት ክፍል 3 ይቀጥላል